# ስለ ሰሞኑ ወሬ ፡ አይ ኤም ኤፍ እና ዲቫሉዌሽን ትንሽ ልሞዳሞድ

<u>የአይ.ኤም ኤፍ ትግል ዝም ብላ የምትታለብ ከብት አንድትኖር የማድረግ አላማ እንዳይሆን አብረን  እንመርምር።</u>



ሰሞነኛው ወሬ ኢትይጵያ የአዬሜፍ የዲቫሉዌሽን ሃሳብ ተቀብላለች የሚለው አንዱ ነበር፡ ጎን ለጎም የግብፅ እና ኢትዮጵያ የናይል ወሃንና የመፃኢው ታላቁ ህዳሴ ግድብ በተመለከተ አንዳንድ ጉዳዮች በይዘታቸው ተደጋጋሚ የሆኑ አርእስቶች እየተንሱ መነጋገርያ ሆነዋል፡ ሁለቱም ጉድዮች ለምን በአንድ ሳምንት ሊነሱ እንደቻሉ አስገርመውኛል። ያምሆነ ይህ ግን ህዳሴ ግድብ በሚመለከት ብዙ የሚያነጋግር ጎድይ ነው ብየ አላስብም ፡ የዚህ የዲቫሉዌሽን ጉዳይም ቢሆን የሚያነጋገር መስሎ አይታየኝም። ቢሆን በአእምሮየ የሚመላለሱ አንዳንድ ጉዳዮች ስለነበሩ ለምን የማስበውን አልፅፍም በሚል ተነሳሳሁ፡ የተሳሳትኩት ነገር ካለም ከሌሎች እርምት በመውሰድ መመር እንድችል በሚል ቀና አስተሳሰብ ነው።

በውጭ አለም ሲኖር ሁልጊዜም ባይሆን አንዳንዴ ስለ አገር ቤት ወሬ ይናፍቃል፡ አገሩ እንዴት እየሄድ ይሆን የሚሉ ጥያቄዎችም መነሳታቸው አይቀርም። መቸለም ለአመል ነው እንጂ አገር ቤት ተቀምጠው የሚቻላቸውን እያደርጉ ካሉት የተሻለ ምን ማድረግ ይቻላል? ብዙም ኢደረግ የሚቻል ነገር ያለ አይመስለኝም፡  ይኑርም አይኑር እስኪ ትንሽ ለሞዳመድ ፍቀዱልን።

መሞዳሞዱን ስለተፈቀደልን በቅድምያ አመሰግናለሁ።

ትንሽ ለማት የፈለግኩት ፡ ስለነዚህ  ሁለት አለም አቀፋዊ  የገንዘብ ድርጅቶች ነው።

በመጀመርያ እነዚህ ድርጅቶች እንዴት መቸ እና ለምን ተፈጠሩ የሚለው አስቀድመን እንመልከት።

በኒው ሃምፕሻየር, ብሪቶን ውድ በተባለ ቦታ በ 1944 ነው የተመሰረቱት  የተመሰረቱበት አላማ አለም አቀፋዊ የንግድ ትብብር ለማበልጸግ  እና አባል አገራትን በብድር አቅርቦት በማገዝ ንግዳቸውን  እንዲያሻሽሉ ለመርዳት ነው ይላል።

በ1980 ባጋጠምው የንግድ ቀውስ እይ.ኤም ኤፍ ፡ በንግድ ቀውሱ ሳብያ ለትጎዱት አገራትን የማዳን ሰራ በአላማው ጨምሮበት የተለያዩ አባል አገራትን ለማዳን መኩሮዋል፡ የቀውሱ መንስኤ ግን ራሱ ይህ እለም አቀፍ ድርጅት አይ ኤም ኤፍ ስለመሆኑ ብዙ አይነገርለትም፡ የተለያዩ የኢኮኖሚ ተንታኞች ሲናገሩ የችግሩ መንሴ በአይ ኤም ኤፍ የሚደረገው አሳሳች የገንዘብ ትንበያ እና ግምታዊ ገበያ ሰነድ አያያዝ  ነው (ስፔኩለቲቭ ግሎባል ኢኮኖሚ) ይላሉ። ስለሆነም እነዚህ አለም አቀፋዊ የገንዘብ ድርጅቶች ድሃ

አገሮችን ኢኮኖምያቸውን እና እሴቶቻቸውን ያገሬው ሰው በሚጎዳ መልኩ እየሰባበሩ ኢኮኖምያቸውን ሙጥጥ አድረገው እየመዘበርዋቸው ነው ይላሉ ተንታኞቹ። ከሁሉም የሚያሳዝን በተለይም ታዳጊ አገሮችን የሚጎዳው እያንዳንዱ የአይ ኢም ኤፍ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችል አገር በአገራዊ ፖሊሲው ለጦች እንዲያደርግ ጫና ማድረጉ ቀጥለዋል የሚለው ውንጀላ አይሎ ይወጣል፡ ከሚጠቀሱ ጫናዎችና ተቀባይነት የማያገኙት ውስጥ፡ ለትምህርት፡ ጤና፡ አከባቢና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ግንባታ ላይ የሚደርጉ ጫናዎች እኩይ ናቸው ይልዋቸዋል ተንታኞቹ፡ ለንዝህ የሚወጡ በጀቶች አይ ኤም ኤፍ ይቆጣጠራቸዋል ፡ አይ ኤም ኤፍ ይወስንላቸዋል ይላሉ፡ አነዚህ ጉዳዮች ለአንድ አገር ህልውና ከምያስፈልጉ ወሳኝ ጉዳዮች ሲሆኑ ግን ትርፍ አስገኚ አይደሉም ። በአይ ኤም ኤፍ ስሌት ተፈላጊ አይደሉም፡ ምክንያቱም አይ ኤም ኤፍ ትርፍ ተኮር ነውና፡ በነዚህ ሴክተሮች የሚወጣው ወጪ ተጠቃሚ አገራት እንዲቀንሱና የአይ ኤም ኤፍን የብድር እዳ እንዲከፍሉ በአይ ኤም ኤፍ ይመከራሉ፡ ይገፋፋሉ። በአጠቃላይ ጉዳዩ ስመረመር እነዚህ ድርጅቶች ዘመናዊ ኢኮኖምያዊ ኮሎኒያሊዝም ወይም ዘመናዊ ባርነት ከማስፍፋት የተለይ አላማ የላቸውም ይልዋቸዋል ተንታኞቹ።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሰው እነዚህ ድርጅቶች የሚገልፅ ሲስሆን አስኪ የተለያዩ ኢኮኖሚስቶች የሚጠቅሱዋቸው ችግሮችን አንድ በአንድ እንመልከት።

1. ዲቫሉዌሽን ኤክስፖርት ያሳድጋል በሚል ስሌት ገንዘብን በተደጋጋሚ ዲቫሉዌት እንዲደረግ መገፋፋት፡ ይህ እንዲሁ ከውጭ ሲታይ ጥሩ ሊመስል ይችላል ፡ ዲቫሉዌሽን ኤክስፖርትን ሊያሳድግ እንደሚችልም ጥርጥር የለውም። ሆኖም ግን ፡ በአብላጫነት የሚጠቅመው ኢምፖርት የሚያድርጉትን ነው ፡ ምክንያቱም በኢኮኖሚ የበለጸጉትና ህብረተሰባቸውን ከሊቅ አስከደቂቅ ያስትማሩት ሃብታሞቹ አገራት በትንሽ ዋጋ የፈበረክዋትን ቴክኖሎጂ ፡ ለታዳጊ አገር የአገር ግንባት ያን ያህል ጥቅም የሌላት ብትሆንም ፡ ግን በከፍተኛ የማስተዋወቅ ሰራ እና በማግባባት ፡ ያገርን መርት ጋር ሲነፃጸር በጣም ውድ በሆነ ዋጋ ይሸጡልህና፡ አመት ሙሉ የለፋህበትን ምርት፡ ብራቸው ጠንካራ ንነው ብለው በተዘዋዋሪ ስላሳመኑህ ብቻ ምርትህን በርካሽ ይገዙታል፡፡ ይህ በጣም ቀላል ስሌት ነው፡ ለምሳሌ አንድ ብዙም የማይጠቅም የኤለኢክትሮኒክስ እቃ፡ የመሸጫ ዋጋና የማምረቻው ዋጋ ከ አገር ቤት ጥሬ እቃ ጋር ማምረቻና መሸጫ ዋጋ ሲወዳደር ልዩነቱ እጅግ በጣም ሰፊ ነው።

   ስለሆነም ዲቫሉዌሽን በተደጋጋሚ እየተደረገ ሲሄድ አገራዊ ሃብትን ዋጋ እያሳጣ ፡ በእዳና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ወድመትን እያፋጠን ይሄዳል፡፡ ከባብያዊ ባለሃብትም እያነሰና እየወደቀ ይሄዳል።

2. አይ ኤም ኤፍ ከአፈጣጠሩ ሃብታም አገሮችን በይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርግ አጀንዳ አንጂ ለድሃ አገራት የቆም ድርጅት አይደለም ሲሉም

ይወነጅሉታል ድርጅቱን፡ በአይ ኤም ኤፍ አደረጃጀት የውሳኔ ሰንሰለቱ በአጠቃላይ ሃብታም ከሚባሉት ወይም በቴክኖሎጂ በበለፀጉት አገራት የተያዘ ነው፡ ምክንያቱም ድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ በያንዳንዱ አባል አገራት አንድ ድምፅ ለአንድ አባል አገር ስሌት ሳይሆን፡ ባለ ብዙ ገንዘብ ብዙ ድምፅ ያገናል በሚል ነው የሚሰራው። ይህም የሚደረገው አይ ኤም ኤፍ ያሰቀመጠው ኮታ ላይ አያንዳኑ አባል አገር የከፈለው የገንዘብ መጠን መሰረት ድምፅ ሰጪነቱ ይወሰናል በዚህ ስሌት አሜሪካ ትልቁ ድምፅ ይዛ ትገኛለች፡ ይህውም 18% ነው፡ ጀርመን፡ ጃፓን፡ ፈረንሳይ፡ እንግሊዝ ተደማምረው ደግሞ 20% ይይዛሉ በአጠቃላይ እነዚህ 5 አገራት 38% ድምፅ አላቸው።

3. የልማት ፕሮግራም አስተሳሰባቸው ኤክስፖርት በማበረታታት ብቻ ያተኮረ ስለሆነ ፡ ለውጭው አለም ይኸውም ለኤክስፖርት ተብሎ የሚመረት ምርትን ነው የሚበረታታው፡ ስለሆነም አገራዊ አቅርቦትን ይጎዳል፡ እዚህ ልብ ሊባል የሚገባው ኤክስፖርት ማሳደግ የለብንም ወይም አይጠቅምም ማለት አይደለም፡ ትክክል ነው ኤክስፖርት አለም አቀፋዊ የንግድ ሂሳብ ስሌታችንን ይስተካክልናል ማለትም ከውጭ የግዴታ የምናስገባውን ፍጆታ ለመግዛት የሚያስችለን የውጭ ምንዛሬ እናገኝበታለን ፡ ይኸውም በተቻለ መጠን ኤክስፖርት በማሳደግ ማግኘት ይኖርብናል ማለት ነው፡። ኤክስፖርት በማሳደግ ብቻ በተለይም ምርቶቻችንን ርካሽ በማድረግ የሚገኝ የኤክስፖርት ገቢ እድገት ወደር የማይገኝለት መትሄ ነው ብሎ ማሰብ ግን የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው፡፡

ስለሆነም ይህ የተሳሳተ የአለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅቶች ስሌት ለወደፊቱ ጎጂ እንጂ ጠቃሚ አይደለም፡ ስለሆነም ልብ ብለን ልናስብበት የሚገባ ጉዳይ ይሆናል፡ ኤክስፖርት እንደ አንዱ የኢኮኖሚ መሰረት ማደግ አለበት ሌሎች የኢኮኖልሚ መሰረቶችም ጎን ለጎን በተመጣጠነ ማደግ ይኖርባቸዋል ። ይህ የነ አይ ኤም ኤፍ ወደ አንድ በኩል ያዘነበለ እና ሚዛኑ ያልጠበቅ ያላደጉ አገሮችን ለቀጣይ ምዝበራ የሚያጋልጥ አካሄድ ግን ሊጠቅመን የሚችል ጉዳይ አይሆንም።

4. ሌላው እነዚህ አለም አቀፍ ድርጅቶች የሚወቀሱበት ጉዳይ የግልፅነትና ተጠያቂነት ጉዳይ ነው።

እነዚህ አለም አቀፋዊ ድርጅቶች ግልፅነትና ተጠያቂነት በያንዳንዱ ተበዳሪ አገር እንዲኖር ይመክራሉ ይገፋፋሉ ፡ ተበዳሪ አገራት መንግስቶቻቸው በኢኮኖሚ ግንባታ ውሱን ድርሻ እንዲኖረው የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በገበያ መርሆዎች ብቻ እንዲተዳደር፡ ለአገር ተብሎ መንግስታት የሚያደርጉዋቸው ዝግ ወሳኔዎች ግልጽ አድርግዋቸው፡ ህዝባቹ ይወቀው ሲሉ ይጠይቃሉ።

በግልባጩ ግን እያንዳንዱ በአገራት ላይ የሚያደርጉዋቸው ውሳኔዎች ለማንም ግልፅ ባልሆነ ከመጋረጃ በስተጀርባ የሚወሰን ውሳኔ ነው። ምንም አይነት ግልፅነትና ተጠያቂነት በሌለበት የውሳኔ ሰንሰለት ሁሉም ነገር ይከናወናል። በተለያየ ጊዜ የቀረበላቸው በሶተኛ ወገን ምርመራ አንቀበልም ብለዋል፡ የሚደረጉ ስብሰባዎቻቸው ለአለም ህዝብ ግልፅ እንዲደረጉ፡ ታክስ ከፋዩ ህብረተሰባቸው አንድያውቀው ይደረግ ተብለው ሲስጠየቁም ፈቃደኛ ሆነው ግልጽ ሊያደርጉ አልሞከሩም ። ታድያ ይህ ትልቅ የግብዞች አሰራር አይደለም?

5. ሃያላን አገራት ያሉ ገበሬዎች በአገራቸው መንግስ የዋጋ ቅነሳ ተጠቃሚ ሲሆኑ ። የአይ ኤም ኤፍ ብድር ተጠቃሚ ለመሆን በራስህ መንግስት የሚደረግልህ የዋጋ ቅነሳ እና ማበረታቻዎች ግን ክልክል ናቸው፡ ለምሳሌ 50% የሚሆን የሄይቲ የሩዝ ገበያ በ አመኤሪካን ሩዝ አምራችና አቅራቢ ገበሬዎች ይሸፈናል የአሜሪካ ገበሬዎች በመንግስታቸው የመንግስት ዋጋ ቅነሳ ተጠቃሚዎች ናቸው፡ የሄይቲ ገበሬዎች ግን አገራቸው ለገበሬዎቹ የዋጋ ቅነሳ እንዳታደርግ በ አይ ኤም ኤፍ ህግ ትከለከላለች ፡ የዋጋ ቅነሳ ስራ ከሰራች የአይ ኤም ኤፍ ብድር ተጠቃሚ አትሆንም ማለት ነው፡፡

በአንፃሩ ደግሞ የተለያዩ የአሜሪካ ኩባንያ ሰራተኞች በአይ ኤም ኤፍ ምክንያት እንደተጎዱ እንደሆነም ይነገራል፡ በለተለይም በሩቅ ምስራቅ በሚደርስ ያለው የሰራተኞች ጉልበት ምዝበራ ምክንያት ፡ በነዚህ አገራት የሚመረቱ ምርቶች ከአሜሪካውያን ዋጋ ሲወዳደር በጣም ስለሚራራቅ አሜሪካውያን ሰራተኞች ከገበያ ውጭ ሊሆን አስችሏል ሲሉ ይወነጅሏቸዋል፡፡

እነዚህንና የመሳሰሉትን ብዙ ችግሮች የኢኮኖሚ ጠበብት ነን የሚሉ ይናገራሉ በተቃራኒውም አይ ኤም ኤፍን ደግፈው የሚከራከሩ አይጠፉም፡ ዋናው ጉዳይ እና ይህንን እጭር ፅሁፍ ለመፃፍ ያነሳሳኝ ግን ፡-

ምናልባት እነዚህ አለም አቀፋዊ የገንዘብ ድርጅቶች ማንነት የማያውቁ ካሉ እንዲያውቁት ከማድረግ በተጨማሪ ፡ በዚሁ የዲቫሉዌሽን ጉዳይ ተያይዞ ሊሆን የሚገባውን የምለውን ሃስቤን ለምሰንዘር እና ከማን አንሼ አስቲ እኔም ትንሽ ልሞዳሞድ በማለት ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ፡ ፕሮፌሰር እከሌ ፡ ዶክትር እከሌ የተባሉ እንዲ ሲሉ ፅፈዋል የሚለውን የምእራባዋያን ሃሳብ እንደገደል ማሚቶ ተመልሰው በኢትዮጵያዊ እንግሊዘኛ አንዳንዶቹ ሊነግሩን ስለሚሞክሩ እኔ ደግሞ ጉዳዩን በተቻለኝ አቅሜ የገባኝ ያክል የራሴን አስተሳሰብ መላው ህብረተሰብ በሚገነዘበው ቁዋንቁዋ ሃሳቤን ለማካፈል ነው።

ስለ አይ ኤም ኤፍ እና ዲቫሉዌሽን ትሩፋት ሰበቡ እንደገባኝ ከሆነ ፡ ብር ዲቫሉዌት ሲስደረግ ብሩን እና የምያድገው የኤክስፖርት መጠን ብቻ ካየን ልንሳሳት እንችላለን የሚል ግምት አለኝ ፡ በመጀመርያ ደረጃ ባለንበት የኢኪኖሚ ፍልስፍና ብር ማለት የአንድ ኢኮኖሚ ብርታት መገለጫ ህጋዊ ሰነድ እንደሆነ ሁላችንም እንግባባለን፡ ብራችን

ዲቫሉዌት ሲደረግ እውነት ነው ያመረትነው ማንኛውም አይነት መርት በአለም ገበያ በአለማቀፋዊ ብር የሆነው ዶላር ተተምኖ ሲቀርብ ርካሽና በሸማቾች ተመራጭ ያደርገዋል፡ ወደውጭ የምርት ሰደዳችንም ያሻሽለዋል፡ የኤክስፖርት ገቢ ይጨምራል፡፡ በነገራችን ላይ ግን ብር ዲቫሉዌ ሲደረግ ዋጋው እየወረደ ያለው ምርቱን የሚያመርት ጉልበት እና እውቀትን ነው ምክንያቱም ዞሮ ዞሮ ዋጋችን የሚተመነው በዶላር ስለሆነ ነው፡ ያም ማለት አንድን ስራ ለማከናወን የምናጠፋት እያንዳንድዋ ሰአኣትና ፡ ጉልበት፡ በአጠቃላይ የአገሪቱ ሃብት ዲቫሊዌት ባደርግነው ስሌት መጠን እሴቱ ይወርዳል፡፡ ስለዚህ አይ አኤም አኤፍ እያለን ያለው ማንኛውም አይነት ጉልበት፡ እውቀት እና የተፈጥሮ ሃብት ከበለጸጉት አገሮች ጋር ካለው ሲነፃፀር የናንተው እሴት ዝቅተኛ መሆን አለበት ነው፡፡

ትክክል ነው በቴክኖሎጂ፡ በ እውቀት፡ በአንዳንድ የተፈጥሮ ህብት ይዘት ከኛው የተሻሉ እንደሆኑ ለመገንዘብ አያዳግትም ፡ በአጠቃላይ በሁሉም ነገር ከኛው የተሻሉ ናቸው ማለት ግን ትክክል ሊሆን አይችልም።

ስለሆነም የኔ አስተሳሰብ በዋጋ ርካሽ ሆኖ መገኘት ብቻ ኤክስፖርት ያበረታታል የሚባለው የአይ ኤም ኤፍ አባባል ፡ ለቆሙለት ሃብት ተካፋይ ክፍል ሊረዳ የሚችል የአላማቸው ማሻሻጫ ቃል ነው እንጂ፡ ታዳጊ አገሮችን የሚጠቅም አና ለኤክስፖርት አድገት ብቸኛን ወሳኝ መፍትሄ ሊሆን አይችልም ፡ ለምሳሌ ኢትዮጵያ አሁን ባለው አቅም እና ብቃት የቴለፎን ቴክኖሎጂን ፈብርካ በአለም ገባያ ለመወዳደር አስቸጋሪ ሊሆንባት ቢችልም ፡ ጤነኛና የተፈጥሮ ማርን፡ ቡናን፡ የዘይት እህሎችን፡ እና ሌሎች ምርቶችን በብቃትና በጥራት ይዛ በመቅረብ ውጋውን ሳታራክስ ተወዳዳሪ ሆና በጥሩ ዋጋ ለመሸጥ የማትችልበት ምንም ምክንያት አይኖርም፡ አንዲህ አንዳታደርግ ያለው ችግር ግን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡ ስትስንዳርድ በሚል ስሌት በተለያዩ አገራት የተቀመጡ ህጎች ሰብሮ ለመግባት አስቸ የሆነ ጉዳይ መሆኑ መታወቅ ይገባዋል፡ ይህ የስታንዳርድ ጋሬጣ የተለያዩ አገራት የአገራቸውን አምራች እንዳይጎዳ ታስቦ የወጣ ህግ እንደሆነም መዘንጋት የለብንም፡ እነዚህ ስታንዳርድ ተብለው የተቀመጡ በትክክል የኛ ምርቶች ከደርጃቸው የወረዱ ስለሆኑ አይደለም ውድቅ የሚሆኑት፡ እነዚህ አገራት በተለያየ ጊዜ የራስቸውን ጥቅም በተለይም የአገር ውስጥ ምርታቸውና አምቾቻቸው እንድይጎዱባቸው ሲሉ ያስቀመጥዋቸው ህጎች ናቸው ለምሰበርም አዳጋች የሚሁኑት ለዚህ ነው። አነዚህን ጉዳዮች በተለይ የሃያላን አገራት ያወጥዋቸው ስታንዳርድ የሚባሉት እንደ አይ ኤም ኤፍ የመሳሰሉ ድርጅቶች ጥቅም የሚያገኙበት ስላልሆነ ሊያስቀዩርዋቸው አይችሉም፡ አይሞክሩምም።

ሌላው እንቆቅልሽ፡ አገር ተኮር የሆነ የኢኮኖሚ ልማት ለመምራት ሲሞከር በተለይም በውጭ ገበያ አገርህ እንዳይጎዳ እነሱ ስትናዳርድ የሚሉት አየነት ተከላካይ የንግድ ፖሊሲ በሚኖርበት ወቅት ተከላካይ (ፕሮቴክሺንስት) ኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው የሚል ተቀፅላ ይወጣለታል፡ በአንድ ወቅትም ጎረቤታችን የሆኑት ፕረዚደንት ኢሳያስ አፈውረርቂም ከጸቡ በፊት ወያኔ ፕሮቴክሽኒስት ነው ብለው የአቅማቸው ያህል በማናናቅ አይነት

ወርፈውናል፡ አሁን ጠቅልለው በራቸው መዝጋታቸው ላይቀር።በጣም የሚገርመው ጉዳይ ግን ፡ በሃያላን አገራት እና በነ አይ ኤም ኤፍ የሚወደሱት አገሮች ውስጥ ነፃገበያን የሚፃረረ የሚባለው ተከላካይ የኢኮኖሚ ፖሊሲ (ፕሮቴክሽኒስት) በያንዳንዱ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቻቸው ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌለው ምሳሌ ማውጣት ስሚቻል ነው።

ለነገሩ ነው እንጂ ጩቤ ሰው አይጎዳም የሚሉት አባባል አለ፡ እስካሁን ዲቫሉዌት እንዲደረግ ሲጠይቁ ፡ ጫና ሲያደርጉ ዲቫሉዌት ሲደረግ ቆይተናል ፡ የአገራችን ብር በጀንያ ተሽከመን ብንሄድም ምንም አልሆንም፡ የአገሩ ኢኦኖሚ በአንጻሩ የተረጋጋ መሆኑም አስመስክሮዋል፡ ከአሁን ወዲህ የዲቫሉዌሽን ምክር ብዙም ባንጨነቅበት ይሻላል የሚል እምነት አለ፡፡

ምሳሌ አንውሰድ፡ አሁን በግንባታ ላይ ያለው የኤሊክትሪክ ማመንጫ ግድብ ብር ለማግኘት በአገር ደረጃ ያጋጠመው ውጣ ውረድ የማይረሳ የታሪክ ሃቅ ነው፡ ምነው ያኔ አይ ኤም ኤፍ ለግድቡ ብር እንስጣቹ ብዙ አትጨነቁ ፡ በውሃላ ዲቫሉዌት አድርጉ ስንላቹ እሺ በሉን ያላሉን። የት ትደርሳላቹ በሚል ጀሮ ዳባ አይደለም እንዴ ያሉት ፡ አልፎም ተርፎም ጥቂት የጩሀት ፖለቲከኞችን ውስጥ ለውስጥ በማነሳሳት የአገሪቱ ጉዳይ የአንድ ግለሰብ ወይም የአንድ ድርጅት ጉዳይ በማስመሰል ፡ አንዴ ቻይናን እናወግዛለን በሉ ብለው በዲሲ ከተማ ዳንኬራ ሲያስመቱዋቸው ፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ የተሃድሶ ግድብ ግንባታ የሚያስከትለው የተፈጥሮ ሃብት ውድመት አለ ሲባል፡ ሲያደንቁሩን ሰንብተዋል።

በተግባሮቻቸው ዙርያ ብዙ ገጠመኞች መተረክ ይቻል ነበር ፡ ሆኖም ግን ተቻችለን በሚረዳቸው መንገድ እና በአጽንኦት ለምክራቹ እናመሰግናለን ፡ የማያዋጣን ጠማማ ጉዞ ስለሆነ ግን አንመርጠውም ብሎ መንገሩ ተመራጭነት ያለው ጉዳይ ነው።

እንደ ሃገር ማድረግ የሚገባን አገርና ህዝብን በቅድምያ ሊጠቅሙ በሚችሉ ነገሮች ላይ ማተኮርን ነው፡ ከፍተኛ የሆኑ የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎች ተሰርተዋል፡ በመሰራትም ይገኛሉ ይበል የሚባልለት ስራ ነው፡ በኤክስፖርትም ቀላል የማይባል ገቢ እየተገኘ ነው፡ ከዚህ በላይ ማግኘትም ይቻላል፡ ሊገኝ የሚችለው የኤክስፖርት ገቢ አይ ኤም ኤፍ በሚለው ይምክር ስሌት ብቻ አይደለም፡ አይ ኤም ኤፍ ተንታኞች ከራሳቸው የረዥም ጊዜ ጥቅም ይህንን ምክር ሊመክሩን ይችላሉ ሆኖ ም ግን ብቸኛ እና ወነኛ አማራጭ ነው ማለት ግን አይቻልም፡ ዲቫሉዌሽን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አገሪትዋ ርሳዋ ስሌትዋን አስልታ ልናደርግ ትችል ይሆናል የሚደረግውም ኤክስፖርት ሊያሳድጉ የሚችሉ ሁሉም አማራጮች መፍትሄዎች አሚጠን ከጨረስን በውሃላ የሚመጣ የኢኮኖሚ መርህ ነው እንጂ ብቸኛው አማራጭ እና ኣሁን የግድ መደርግ የሚገባው መፍትሄ ነው ማለት አይደለም።

በስፋት ኤክስፖርት ለማሳደግ ታድይ ምን ማድረግ ይቻላል?

1. ከአለም አቀፍ ቴክኖክራትና ፡ ቢሮክራስያዊ የስታንዳርድ ማነቆ ለዘብ ያሉ የአገራችንን ምርት ተጠቃሚ የሆኑ አገራትን ለይቶ በዝርዝር ማውጣት፡ ይህም

ከመንግስት ይጠበቃል፡ ይህ ሲባል እነዚህ የገበያችን ዋና ተመራጭ ተብለው ሊሰየሙ ይችላሉ፡ ሌሎቹም ጭምር፡፡

2. ለኤክስፖርት የምንመርጣቸው ጥሬ ሃብቶች ምርታማነታቸው በድርብ እጥፍ ለማሳደግ መፍትሄ ማፈላለግ፡ ምርት ከማሳደግ ጎን ለጎን ጥራታቸው አስከተቻለ ድረስ ማሻሻል፡ ከዛም ባሻገር ሸማቾች እንደሚሉት ሳይሆን ፡ በራስ ምርት መተማመን፡ ምክንያቱም ስለራሱ ምርት ሊያውቅ የሚችል ባለቤቱ ነው ማንም ሊያውቅለት አይችልም፡ ስለምርትህ ጥራትና ብቁነት በልበ ሙሉናት ደረትህን ነፍተህ መናገር መቻልም ይጠይቃል፡፡ እንደ እኔ ግንዛቤ ከሆነ ማንኛውም የአገራችን ምርት ከማንም የበለጠ እንጂ ያነስ ሊሆን አይችልም ። በአገር ውስጥ ጥራት የጎደለው ሲገኝ ሃላፊነት በተሞላ እንዲሻሻል በሚል ስሌት እንዲሻሻል በግልፅ መንቀፍ እንዲሻሻል ማድረግ፡፡ የአንዱን ምርት ለማጣጣል ወይም የማትወደውን ለመጉዳት ግን መሆን የለበትም፡፡

3. አለም አቀፋዊ የኤክስፖርት ኔትዎርክ መፍጠር፡ይህንንም እንዲበረታታ መገፋፋት። ይህም ኔትወርክ የአገርን ምርት ማስተዋወቅያ፡ የአገርን እሴቶች ማሳወቅያ፡ እሴቶቻችን ከረኣሳችን ተርፈው ለሌላ ሊሆኑ እንድሚችሉ ራሳችን ከልብ አምነን፡ ሌላውን አለም ማሳወቅ። ሌላው አለም ለእሴቶቻቸው ዋጋ እንደሚሰጡ የኛም ዋጋ እንዳለው መተማመን፡ በዛም ረግቶ መኖር ይጠይቃል፡፡

4. የአለም ገበያ ጥናት ሲስደረግ አብዛኛው ጊዜ ዋና ሸማች እና ጥቅም ይገኝላቸዋል ተብለው የሚወሰዱት ሃብታም አገራት ናቸው ይህ ግን ሁልጊዜ እውነት አይደለም፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ተጠቃሚ ሊሆኑ ከሚችሉ አገራት ሱዳን፡ (ሰሚኑን ደቡብ) እና ግብፅ ናቸው። ስለሆነም ከነዚህ ሁለት አገሮች ከምእራቡ አለም በማይተናነስ በባቄላ መርት ገቢ ማግኘት ይቻላል፡፡ በሎቄ ብንወስድ፡ በስፋት ለኤክስፖርት ብናመርት ቻይና ትልቁ ገበያ ነው፡ እና ከአሜሪካና ጀርመን ምን ያዳርቀናል ለማለት ነው፡፡

በከፊሉ ከዲቫሉዌሽን ተያይዞ ለመጻፍ የፈለግኩት ይህ ሲሆን፡ በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ፍልሰፍናችን መሆን የሚገባው የተፈጥሮ ሃብታችን እና ያገራችን እሴት ማሃል ያደረገ መሆን ይገበዋል እንጂ ብር እና ብርን ማሃል ያደረገ መሆን የለበትም፡ ይህ ስል እስከአሁን ያለው ብር ማሃል ያደረገ ነው የሚል ወቀሳ ለመሰንዘር አይደለም፡ በነ አይ ኤም ኤፍ እና የመሳሰሉት የሽወዳ አቀራረቦች እንዳንሸረሽር ለማለት ያክል ነው። የጨሁት ፖለቲከኞቻችንም ፡ አትሰልቹን የሽወዳ ዳንኬራው በቃ እባካቹ፡ ስራ ክቡር ነው ፡ አገር ህዝብ የሚጠቀመው በስራ ታታሪነት ፡ ከልብ አገር በመውደድ እንጂ ፡ በስልታን ኮርቻ ለመጠላጠል በፖሌቲካ ቃላት ስንጠቃ እስክስታ ብንመታ ጠብ የሚልልን ነገር ሊኖር አይችልም በማለት መሞዳሞዴን እዚህ ላይ ላብቃ፡፡

**አገራችን ሰላም፡ ብልፅግና እና ተስፋ አይለየው፡፡**

**ሙሉብርሃን ዳኘው**

08-29-14